የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሀረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 28ኛ ዓመት ቁጥር 1<br>28th Year No. 1 | | ሀረር ሀምሌ 27 ቀን 2014 ዓ.ም<br>HARAR, August 3/ 2022 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 40:00<br>Unit Price Birr 40 :00 | በሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 952<br>P.O.Box 952 |

ማውጫ

የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ———————————————— ገጽ 1444

## አዋጅ ቁጥር 156/2014

## የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በተለያዩ አካላት በተበታተነ ሁኔታ ሲሠራ የነበረውን የዐቃቤ ሕግ ተግባር በአንድ ላይ በማቀናጀት ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ተደራሽ እንዲሁም የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን በአንድ ተቋም ስር ተደራጅቶ ያለውን ውጤታማና ቀጣይነትነቱን ማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቱን በመወሰን የተጠናከረ ተቋማዊ አሰራር እንዲሰፍን መደረግ እንዳለበት በመታመኑ፤

ሕጎች በሚገባ መደራጀታቸውንና የመንግስት ሥራዎች በሕግ መሰረት መመራታቸውን የሚያረጋግጥ እንዲሁም የሕግ የበላይነትን የሚያስከብር ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ፤ የሕዝብንና የመንግስትን ጥቅም በተሟላ ሁኔታ የሚያስጠብቅ አንድ ጠንካራ ሕግ አስከባሪ የዐቃቤ ሕግ ተቋም ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የሕዝብ ተዐማኒነት ያለው፣በተሟላ ተቋማዊና ሙያዊ ነፃነት የሚያገለግል እንዲሁም ለሙያዊ፣ ተቋማዊና ሕዝባዊ ተጠያቂነት የሚገዛ፣ በግልጽነትና በአሳታፊነት የሚሰራ የዐቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 2 (ሀ) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሀረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 156/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

1.«**ሕገ-መንግስት**» ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና/ወይም የተሻሻለው የክልሉ መንግሥት ሕገ-መንግስት ነው፤

2.«**ክልል**» ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ቁጥር (9) መሠረት የተቋቋመው የሀረሪ ሕዝብ ክልል ነው፤

3. **«ምክር ቤት»** ማለት በክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተቋቋመና የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የህግ አውጪ አካል ነው፡፡

4.**«መስተዳድር ምክር ቤት»** ማለት በክልሉ መንግስት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

5.**«ፕሬዝዳንት»** ማለት የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዝዳንት ነው፤

6.**«የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች»** ማለት ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግስት በጀት የሚተዳደሩ አካላት ሆነው የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶችንም ይጨምራል፤

7.**«ሕግ»** ማለት በፌድራል መንግስቱ ሕግ አውጪ ወጥተው በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸው የሕግ ማዕቀፎችን፣ በክልሉ ሕግ አውጪ አካላት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና ስልጣን በተሰጣቸው የክልሉ መንግስት አካላት የወጡ መመሪያዎችን ያጠቃልላል፤

8.**«የወንጀል ሕግ»** ማለት ማንኛውም በፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በክልሉ ምክር ቤት የተደነገገ የወንጀል ሕግ ነው፤

9.**«የሙስና ወንጀል»** ማለት በ1997 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የወንጀል ህግ፣ በፌዴራል የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 እና በሌሎች ህጎች የሙስና ወንጀል ተብሎ የተደነገገው ነው፤

10.**«የታክስ ወንጀል»** ማለት የወንጀል ሕግን ወይም የታክስ ሕጎችን በመተላለፍ በግብር እና ታክስ ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ተግባራት ማለት ነው፤

11.**«ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ»** ማለት የክልሉ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ነው፤

12.**«ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ»** ማለት በክልሉ መንግስት ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የተሾመ የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊ ነው፤

13.**«ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ»** ማለት በክልሉ መንግስት ፕሬዝዳንት የተሾመ የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ምክትል ኃላፊ ነው፤

14.**«ዐቃቤ ሕግ»**ማለት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት የሚቀጠር፤ የሚሾም ወይም የሚመደብ እና የሚተዳደር የሕግ ባለሙያ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት የተሾሙትን ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉንና ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን ይጨምራል፤

15.**«ፖሊስ»** ማለት ስልጣን ያለው የክልሉ ወይም የፌዴራል መንግስት ፖሊስ ነው፤

16.**«የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት»** ማለት ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠረት፣ የመንግሥት አካል ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ያልወገነ እና ሕጋዊ ዓላማን ለማሳካት በክልሉ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ሲሆን፣የሙያ ማኅበራትን፤የብዙኃን ማሕበራት እና የድርጅቶች ኅብረቶችን ይጨምራል፤

17.**«ሰው»**ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

18. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>መቋቋም ፤ ተጠሪነት እና ሥልጣንና ተግባር</u>

**3. <u>መቋቋም</u>**

የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ከዚህ በኋላ *«ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ»* እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**4. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዋና መሥሪያ ቤት በሐረር ከተማ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ በክልሉ ባሉ የወረዳ መስተዳድሮች የዐቃቤ ሕግ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

**5. <u>ዓላማ</u>**

ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማክበርና ማስከበር፤

ለ)የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤

ሐ)የወንጀል ሕግን ማስከበር፤

መ)የክልሉን መንግሥት እና የህዝብን የፍትሐብሔር ጥቅም ማስከበር።

## 6. ተጠሪነት

1.የጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ተጠሪነት ለፕሬዝዳንቱና ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ይሆናል፡፡

2.በየወረዳው የሚገኙ የወረዳ ዐቃቤ ሕግ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ሙያዊ ተጠሪነታቸው ለዋናው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ሆኖ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ተጠሪነታቸው ለየወረዳው ዋና አስተዳዳሪ እና ለየወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ነው፡፡

3. በክልሉ በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ ዐቃቤያነ ሕግ የበላይ ኃላፊ ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ነው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በየትኛውም ደረጃ ያለ ዐቃቤ ህግ ለበላይ ኃላፊያቸውና ለተመደቡበት የስራ ዘርፍ ኃላፊዎቻቸው ተጠሪ ይሆናሉ ፡፡

## 7. ሥልጣንና ተግባራት

ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1.በአዋጅ ቁጥር 101/2003 ((በአዋጅ ቁጥር 104/2004 እና በአዋጅ ቁጥር 143/2012 እንደተሻሻለው) እና በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በሥራ ላይ ያውላል፤

2. ሕገ-መንግሥታዊና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤

3. በሕገ-መንግሥትና በሕግ ጥበቃ ያገኙ የዜጎች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

4. በሕግ ጉዳዮች የክልሉ መንግስት ዋና አማካሪ እና ተወካይ ሆኖ ይሰራል፤

5. በክልሉ መንግሥት የሚወጡ ሕጎች ሥራ ላይ መዋላቸውንና አፈፃፀማቸውም ተመሣሣይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤

6. ሐገራዊ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲን ሥራ ላይ ያውላል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤

7. የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ፡

ሀ. በሌሎች ሕጎች ለፖሊስ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር በሚወድቁ በማናቸዉም የፀረ-ሙስና፣ የታክስ ህጎች እና የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅን በመጣስ በሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች እንዲሁም ከባድና ውስብስብ የሆኑ ልዩ ልዩ የወንጀል ድርጊቶችን ጨምሮ በክልሉ ፖሊስ ምርመራ ዘርፍ የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎችን ከፖሊስ ጋር አብሮ ያጣራል፤ ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል

ለ. ለምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግና በሌሎች ሕጎች መሠረት አስቀርቦ ይጠይቃል ፣ቃል ይቀበላል፤ ከማንኛውም ሰው ወይም መስሪያ ቤት ማስረጃ እንዲቀርብ ያዛል፤

ሐ.ምርመራቸው በፖሊስ በተጀመረባቸው መካከለኛ፣ ቀላል እና በግል አቤቱታ በሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ምርመራ በአግባቡ ስለመከናወኑ በቅርበት ክትትል ያደርጋል፤ የተጀመረ የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ ፖሊስ ለዓቃቤ ህግ ማሳወቁን ያረጋግጣል፤

መ.በሕዝብ ጥቅም መነሻ ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠው የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ያደርጋል፤ ማናቸውም የወንጀል ምርመራዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ አስፈላጊውን ህጋዊ ትእዛዝ ለሚመለከተዉ አካል ይሰጣል፤

ሠ.የተጠናቀቁ የምርመራ መዝገቦችን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር መርምሮ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት የተቀመጡ መመዘኛዎች ሲሟሉ የአያስከስስም ወይም የተዘግቷል ውሳኔ ይሰጣል፤

ረ. በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠ የዓቃቤ ሕግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው ፖሊስ ያሳውቃል፣ የወንጀል ምርመራ መዝገቦችን አስመልክቶ በየደረጃው ባሉ ዓቃቤያነ ሕግ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በፖሊስ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሰ. የጥፋተኝነት ድርድር ይወስናል፣ ድርድር ያደርጋል፣ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ይወስናል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሸ. የክልሉን መንግስት በመወከል እንዲሁም በፌድራል መንግሥት በሚሰጥ ውክልና መሠረት የወንጀል ጉዳዩች ላይ ክስ ይመሰረታል፣ ይከራከራል፣ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ ያነሳል፣ የተነሳ ክስ እንዲቀጥል ያደርጋል፤

ቀ. በየደረጃው ባለው ፍርድ ቤት በሚሰጠው ፍርድ ላይ ቅሬታ ካለ ይግባኝ ይጠይቃል፤ ይከራከራል፤ የሰበር ማመልከቻ ያቀርባል፤

በ. የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በህግ መሰረት ጥበቃና ከለላ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ተ.በፖሊስ ጣቢያና በማረሚያ ቤት ቁጥጥር ሥር ያሉ ተጠርጣሪዎችና ታራሚዎችን ይጎበኛል፣ አያያዛቸው እና ቆይታቸው በሕግ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፣ ሕገወጥ ተግባር ተፈፅሞ እንደሆነ እንዲታረም ያደርጋል፤ ሕግን ተላልፈዋል በተባሉ ሰዎች ላይ በሕግ መሰረት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ቸ.በዕርቅ ሊያልቁ የሚችሉ የወንጀል ድርጊቶች በእርቅ የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ነ. በፍርድ ቤት የሚወሰኑ የወንጀል ቅጣቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ያደራጃል ወይም መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤

አ. የሞት ቅጣት ውሳኔዎችን ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በፍትህ ሚኒስተር በኩል እንዲቀርብ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

8. የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ:

ሀ. ለክልሉ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ ለሕዝብ እና ለመንግስት መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ ይከራከራል፣ ያስከብራል፣ እንዲከበሩ ያደርጋል፣ የሚከበሩበትን ሂደት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ. ትላልቅ የመንግስት ፕሮጀክቶችን የውል ዝግጅት እና ድርድር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያደርጋል፣ የሕዝብና የክልሉን መንግስት መስሪያ ቤቶች ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን በሌሎች ጉዳዮች ውል እና የመግባቢያ ሰነዶች ዝግጅትና ድርድር ያደርጋል ወይም የሚመለከታቸውን አካላት ያማክራል፤

ሐ. የክልሉን መንግስት መስሪያ ቤቶች በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ይመሰርታል፤ በከሰሱበት ወይም በተከሰሱበት የፍትሐ-ብሔር ጉዳዮች ላይ ክርክር ያደርጋል፤ በተጀመረ ክርክር ተቋማትን ተክቶ በተናጥል ወይም በጋራ ይከራከራል፣ ወይም በክርክር አመራር ላይ ለመሥሪያ ቤቶች አቅጣጫ ይሰጣል፣ በሕግ መሠረት ለተሰጡ ዉሳኔዎች ፍርድን ያስፈፅማል፤

መ. በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና በግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች መካከል የሚከሰቱ የፍትሐ ብሔር ክርክሮች በድርድር እንዲያልቁ ጥረት ያደርጋል፤ ድርድሩ ካልተሳካ ጉዳዩን ስልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት አቅርቦ ይከራከራል፤

ሠ.የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጭ ባለ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገድ እንዲወሰን የውሳኔ ሀሳብ ይሰጣል፤ በውሳኔው መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

ረ. የተመዘበረ የመንግስት ገንዘብ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ያስመልሳል፡፡ የሙስና ወንጀል ዉጤት የሆኑት እና በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶችን ያስተዳድራል፤ እንዲወረስ ውሳኔ የተሰጠባቸዉን ንብረቶች ለሚመለከተዉ የመንግስት አካል ያስተላልፋል፤

ሰ. የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት የገንዘብ አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን ወክሎ ይከራከራል፤

ሸ. የገንዘብ አቅም የሌላቸው የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ተበዳዮች እንዲካሱ፤ መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲሁም ከጉዳቱ ጋር የተያያዙ የፍትሐብሔር ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እነሱን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ያቀርባል ወይም ይደራደራል፡፡

9. የሕግ ጥናት፣ማርቀቅ እና ግንዛቤ መፍጠርን በተመለከተ:

ሀ. በክልሉ መንግሥት የሚወጡ ሕጎች የሕግ ረቂቅ ዝግጅት ስራ ይሰራል፤ በመንግስት አካላት የሚዘጋጁ ረቂቅ ሕጎች ከህገ መንግሥቱ፣ ከክልሉና ከፌዴራል ሕጎች፣ ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ከሴቶችና ህፃናት መብት እንዲሁም ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ሌሎች ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ለ.በክልሉ በስራ ላይ ባሉ ሕጎች ላይ ጥናት በማድረግ ሕጎች እንዲሻሻሉ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲደገፍም ለተባሉት ማሻሻያዎች ረቂቆችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣

ሐ.ሕጐችን የማሰባሰብ፣ የማጠቃለልና የኮዲፊኬሽን ሥራ ይሰራል፤ የክልሉን ሕጎች በባለአደራነት ይይዛል፣ ያሰራጫል፤

መ. ዐቃቤያነ ሕግ ስለስራቸው ያላቸውን አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት በተከታታይ እና በየደረጃው ለማሳደግ ትምህርት እና ሥልጠና ይሰጣል፤ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፤

ሠ. የህብረተሰቡን ንቃተ ሕግ ለማዳበር ለክልሉ ህብረተሰብ በተለያዩ ዘዴዎች የንቃተ ህግ ትምህርት ይሰጣል፡፡

10.የጠበቆች፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችን እና የሰነድ ማረጋገጥን በተመለከተ:

ሀ. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሚከራከሩ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ስራቸውን ይቆጣጠራል፣ የጠበቆችን የዲሲፕሊን ጉዳዮች አይቶ ይወስናል፤ በህግ መሰረት ይሰርዛል፣

ለ.በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን ይመዘግባል፣ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይደግፋል፣ ሥራቸውን ያሳልጣል፣ ያስተባብራል፤ ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሲሆን በሕግ መሰረት ይሰርዛል፤

ሐ.አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሰነዶችን ይመዘግባል፣ ያረጋግጣል፣ ይሽራል፣ ይሰርዛል፣

መ.አቅም ለሌላቸው ዜጎች ነፃ የሕግ ድጋፍ አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን ይቀርፃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ በመስኩ የሚሰማሩ አካላትን ያስተባብራል፡፡

11.ብሔራዊ የሰብአዊ መብት ድርጊት መርሀ ግብርን መነሻ በማድረግ ክልላዊ የሰብአዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤በክልል ደረጃ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

12.የክልሉን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤ የህግ ታራሚዎች ይቅርታ የሚያገኙበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

13.የዐቃቤ ሕግ የውሳኔ አሰጣጥ እና የሥልጣን አጠቃቀም ወጥነትን ለማረጋገጥ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የፀደቀ መመሪያ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

14.በዐቃቤያነ ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን የሚያረጋግጥ የኢንስፔክሽን ክፍል ያደራጃል፣ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ ይለያል፤ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፣ መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራል፤ ያስፋፋል፤

15. የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈፅማል፤

16.ሴቶችና ህፃናት በፍትህ አስተዳደሩ ውስጥ ተሳታፊዎችና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ይሠራል፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ይደግፋል፤

17. የክልሉን መንግስት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፤ ተጠሪነት፤ ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለማሻሻልና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 101/2003 (በአዋጅ ቁጥር 143/2012 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 10 መሠረት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባል ለሆኑ አስፈፃሚ አካል መስሪያ ቤቶች የተሠጡትን የወል ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

18.በሕግ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ወይም ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**8. <u>ሹመት</u>**

1.ዋናው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል፡፡

2.ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ በክልሉ ፕሬዚዳንት ይሾማል፡፡

3.በየትኛውም ደረጃ የሚሾም ዐቃቤ ህግ በህግ ትምህርት እውቅና ካለው ተቋም የተመረቀ መሆን አለበት፡፡

**9. <u>የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት አደረጃጀት</u>**

ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ፣

1. ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፤
2. የሥራ ዘርፎች፣
3. የማኔጅመንት ኮሚቴ፤
4. የክልሉ ዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ፤
5. በዋናው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቅራቢነት በዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የሚሾሙ ዐቃቤያነ ሕግ እና
6. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**10. <u>የዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1.ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመሆን በሙያውና በሕግ መሠረት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

2.በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. በክልሉ የሥነ - ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 71/1999 እና በተሻሻለው የገቢዎች ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 115/2005 መሰረት ለፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና ለገቢዎች ባለስልጣን መሥሪያ ቤቶች እና ለበላይ ኃላፊዎቻቸው ተሰጥተው የነበሩ ዐቃቤ ሕግነትን የተመለከቱ ሥልጣንና ተግባራትን ሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ. በሕግ ላይ በመመሥረት በምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የዐቃቤ ህጉ ስራን አስመልክቶ የተሰጡ ውሳኔዎችን ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይለውጣል፣ ይሽራል ወይም ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፤

መ. ዓቃቤያነ ህግን በዐቃቤያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ በህግ መሰረት ያሰናብታል፤

ሠ. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤትን ስትራቴጂክ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ረ. ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በተፈቀደለት በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሰ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉት ግንኙነቶች ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ይወክላል፤

ሸ. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፤

ቀ.ለሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ፣ ለዐቃቤያነ ሕግና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

በ. በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**11. <u>የምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ተጠሪነቱ ለዋናው ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1)በዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፤

2)ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ በማይኖርበት ጊዜ ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን ተክቶ ይሰራል፡፡

**12. <u>ከሹመት ስለመነሳት</u>**

ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ እና ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ በፕሬዝዳንቱ ውሳኔ ከሹመታቸው ሊነሱ ይችላሉ፡፡

**13. <u>የዐቃቤያነ ሕግ ሹመት</u>**

የክልሉ ዐቃቤያነ ሕግ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ አቅራቢነት በዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ የሚሾሙ ይሆናል፡፡አፈፃፀሙ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**14. <u>የዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር</u>**

የዐቃቤያነ ሕግ አስተደደር በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

1)የዐቃቤያነ ሕግ ሹመት በሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡-

ሀ. ለሕገ መንግስቱ እና ለሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱ እንዲሁም ለሕግ የበላይነት ያለው ተገዢነት እና እምነት፤

ለ. ሕዝባዊ አገልጋይነት፤

ሐ. ኢትዮጵያዊ ዜግነት፤

መ. ጥብቅ የሥነ ምግባር ሁኔታ፤

ሠ. ለዐቃቤ ሕግ ሥራ አስፈላጊ የሆነ የሕግ ትምህርት ዝግጅት እና ክህሎት፤

ረ. የክልሉን የሥራ ቋንቋ መናገር፤ መፃፍና ማንበብ መቻል፤

ሰ. በዘርፉ እንዳስፈላጊነቱ የሚሰጠውን የቅድመ ሥራ ሥልጠና ተከታትሎ በስኬት ማጠናቀቅ፤

ሸ. የዐቃቤ ሕግ አገልግሎት የሚጠይቀውን ኃላፊነት የመወጣት ቁርጠኝነት፤

ቀ. ዐቃቤ ሕግ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች ገለልተኛ መሆን፡፡

**15. <u>ስለ ክልሉ ዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ</u>**

1.ተጠሪነቱ ለዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሆነ የክልሉ ዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ በዚህ አዋጅ መሰረት እንደገና ተቋቁሟል፤ የጉባኤውን አባላት፣ የአሠራር ሥነ-ሥርዓትና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤

2. የክልሉ ዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ የዐቃቤያነ ሕግ ሹመት፣ ምደባ ፤እድገት ዝውውር፣ የዕረፍት ጊዜ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ ደረጃ፣ ሥነ-ምግባር፣ አደረጃጀት፣ መዋቅር፣ ደመወዝ፣ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እና የመሳሰሉ ጉዳዩችን ያካተተ ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለዋናው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የማቅረብ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የዐቃቤያነ ሕግ የሙያ ነፃነትና ተጠያቂነት</u>

**16. <u>የዓቃቤያነ ሕግ የሙያ ነፃነት</u>**

1.ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባሩን ሲያከናውን ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ በሕግ መሠረት ብቻ ይፈጽማል፡፡

2. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚያወጣው የአሠራር መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በሕግ መሠረት በነፃነት ያከናውናሉ፡፡

3. በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ የዐቃቤያነ ሕግ ተጠያቂነትን አስመልክቶ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉና ምክትሉ እንዲሁም ዐቃቤያነ ሕግ በሕግ መሠረት የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር በማከናወናቸው ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሕግ ተጠያቂነት የለባቸውም፡፡

**17. <u>የዐቃቤያነ ሕግ ተጠያቂነት</u>**

በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ጉድለት ያሳየ ወይም የሥነ-ምግባር ጥፋት የፈጸመ ዐቃቤ ሕግ በህግ ወይም በሥነ-ምግባር ደንብ የሚጠየቅ ይሆናል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**18. አቤቱታ የማቅረብ መብት**

1.ዐቃቤ ሕግ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በየደረጃው ለሚገኙ የዐቃቤ ሕግ ኃላፊዎች አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤ አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊም ጉዳዩን በአፋጣኝ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2. አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊ ጉዳዩን ለማጣራት አግባብ ያላቸውን ባለሙያዎች የሚያካትት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

3.አቤቱታውን የመረመረው ኃላፊ የሕግና የማስረጃ ምክንያቱን በመጥቀስ በበታች ዐቃቤ ሕግ የተሰጠውን ውሳኔ ለማጽደቅ፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ፣ ለመሻር፣ ለማገድ ወይም ጉዳዩን አስቀድሞ አይቶ ወደ ወሰነው ክፍል ለመመለስ ይችላል፡፡

4.በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት በተሰጠዉ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ አካል ቅሬታዉን ደረጃዉን ጠብቆ እስከ ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ድረስ በየእርከኑ ላሉት የበላይ ኃላፊዎች ማቅረብ ይችላል፡፡ ሆኖም የዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**19. ጥቆማ ወይም አስተያየት የማቅረብ መብት**

1.ማንኛውም ሰው በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር ውስጥ የሚወድቅ ማንኛውም መታረምና መስተካከል አለበት የሚለውን ጉዳይ ወይም ተፈጽሟል የሚለውን የሥነ-ምግባርና የሕግ ጥሰት ማናቸውንም አግባብ በመጠቀም ለመስሪያ ቤቱ ወይም በየደረጃው ላሉት መዋቅሮች ጥቆማ ወይም አስተያየት ለማቅረብ ይችላል፡፡

2.የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ጥቆማ፣ አስተያየትና ቅሬታዎችን የሚቀበልበት፣ የሚያጣራበትና የመፍትሄ እርምጃ የሚወስድበት እና ለሕብረተሰቡ የሚገለጽበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**20. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

1.በአዋጅ ቁጥር 101/2003 (በአዋጅ ቁጥር 143/2012 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 29 ሥር የተደነገጉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡

ሀ. የሙስናና የታክስ ወንጀሎችን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 71/1999 እና አዋጅ ቁጥር 115/2005 እና በሌሎች ሕጎች ለክልሉ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና ለክልሉ ገቢዎች ባለሥልጣን እንደየቅደም ተከተላቸው የተሰጠው ጥቆማ የመቀበልና የመመርመር ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ መሠረት ለክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት እና ለክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ተላልፈዋል፡፡

ለ.በክልሉ መንግሥት የሥነ- ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 71/1999 እና በሌሎች ሕጎች ለክልሉ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተሰጥቶ የነበረ የሙስና ወንጀሎችን የመክሰስ ፣የመከራከር እና ውሳኔ የማስፈጸም የዐቃቤ ሕግነት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ተላልፏል፡

ሐ. በክልሉ መንግስት ገቢዎች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 115/2005 እና በሌሎች ሕጎች ለባለስልጣኑ ተሰጥቶ የነበረው የታክስ ወንጀሎችን የመክሰስ ፣የመከራከር እና ውሳኔ የማስፈጸም የዐቃቤ ሕግነት ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ተላልፏል፡፡

**21. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1.በአዋጅ ቁጥር 101/2003 (በአዋጅ ቁጥር 143/2012 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 30 ሥር የተደነገጉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. በፍትሕና ፀጥታ ጉዳይ ቢሮ ፣በክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን እና በክልሉ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የወጡ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር ለማስፈፀም አግባብነት ያላቸው ደንቦች ፤መመሪያዎች እና ማኑዋሎች በሌሎች ደንቦች፤ መመሪያዎች ወይም ማኑዋሎች እስካልተተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

ለ. አግባብነት ያላቸው የተሻሻለው የፌዴራል የፀረ- ሙስና ልዩ የሥነ -ሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ ቁጥር 434/97 (በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለው) ፣የክልሉ ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 71/1999 ፣የተሻሻለው የፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/2007 (በአዋጅ ቁጥር 883/2007 እና በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 እንደተሻሻለው) ፣ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007 በክልሉ በሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች ላይ እንደየ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ ፡፡

ሐ. በዐቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ በመታየት ላይ ያሉ የዐቃቤያነ ሕግ የዲሲፕሊን ክስ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ተላልፏል ፡፡

**22. <u>የመተባበር እና የመፈጸም ግዴታ</u>**

1.ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉና ምክትሉ እንዲሁም ዐቃቤያነ ሕግ በሕግ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት ትብብር የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ ያልሆነ እና ጉዳት የማያስከትልበት ከሆነ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2.ማንኛውም የፖሊስ አባል የዐቃቤ ሕግን የመጨረሻ እና ሕጋዊ ውሳኔ የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

**23. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>**

1.ዋና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉና ምክትሉ እንዲሁም ዐቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በነፃነት እንዳያከናውኑ ጣልቃ የሚገባ ወይም የሚሰጠውን ህጋዊ ውሳኔ የማያከብርና የማያስፈጽም እንዲሁም የመተባበር ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለዉ ህግ በወንጀል ይጠየቃል፡፡

2.ማንኛውም የፖሊስ አባል የዐቃቤ ሕግን የመጨረሻ እና ሕጋዊ ውሳኔ በመቃወም ያልታዘዘ እንደሆነ አግባብ ባለው ሕግ በወንጀል ይጠየቃል፡፡

**24. <u>በጀት</u>**

ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ይተዳደራል፡፡

**25. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

1.ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2.የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**26. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

1.የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2.ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

3.በህግ መሰረት ለህዝብ ይፋ እንዳይደረጉ ከተከለከሉ ሚስጥራዊ ሰነዶች በስተቀር የሚያወጣቸውን መመሪያዎች በማናቸውም መንገድ እንዲታተሙ እና እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡

**27. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚት አይኖረውም፡፡

**28. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ሀምሌ 27 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሀረር, ሀምሌ 27 ቀን 2014 ዓ.ም**

**ኦርዲን በድሪ**

**የሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት**

**ፕሬዚዳንት**